**ዶፊን** (Dauphin)፡
- Dauphin Health Centre (ultra sound only)

**ቶምሰን** (Thompson)፡
- Thompson General Hospital

**ዊንክለር/ሞርደን** (Winkler/Morden)፡
- Boundary Trails Health Centre

**ከተጨማሪ ምርመራዎች በኋላ፣ አብዛኞቹ ሴቶች ጤናማ ውጤቶች ይኖራቸውና ለሚቀጥለው የማጣርያ ምርመራ ቀጠሮ ግን ሊመለሱ ይችላሉ።**

## ተጨማሪ ምርመራዎቹ ጤናማ ካልሆኑስ ምን ይሆናል?

በቁጥር ጥቂት የሆኑ ሴቶች ባዮፕሲ (**'ከአካል ላይ ናሙና በመውሰድ የሚከናወን ምርመራ'**) ያስፈልጋቸዋል። ባዮፕሲ በጡት ውስጥ ከሚገኙ የሴሎች ክምችት ላይ ለምርመራ የሚሆን ናሙና መወሰድ ነው። ከአካል ላይ ናሙና በመውሰድ የሚከናወኑ ሶስት አይነት ዋና ምርመራዎች አሉ፣

- **አልትራሳውንድ ኮር ባዮፕሲ** የእባጭ ስሜት በተሰማ ወይም በ'አልትራሳውንድ" በታየ ጊዜ፣ ከሴሎች ክምችት ላይ ለምርመራ የሚሆን ናሙና ለመውሰድ፣ መርፌን ይጠቀማል።
- **እስቴሪዮታክቲክ ኮር ባዮፕሲ** አንድ አከባቢ በጡት ራጂ ('ማሞግራም') ብቻ በታየ ጊዜ፣ ከሴሎች ክምችት ላይ ናሙና ለመውሰድ፣ መርፌን ይጠቀማል።
- **ሰርጅካል ባዮፕሲ** በጡት ውስጥ ከሴሎች ክምችት ላይ ለምርመራ የሚሆን ናሙና በመውሰድ፣ በቀዶ ሕክምና ሐኪም በኦፕራስዮን ክፍል ወይም በክሊኒክ ውስጥ የሚከናወን ነው።

## በተከታታይ ምርመራዎቹ ላይ ነቀርሳ ቢገኝባቸውስ?

የጤና ባለሙያዎ እነዚህን የምርመራ ውጤቶች ከተቀበለ በኋላ፣ እንክብካቤ የሚያገኙበትን ሁኔታ ያመቻቻል።

ማንም ሰው የጡት ነቀርሳ እንዳለው ማወቅ አይፈልግም። ቀደም ብሎ ውጤትን ማወቅ ግን ለቀለለ ህክምና እና ለመዳን የተሻለ ዕድል ይሰጣል።

**ተጨማሪ መረጃ ካስፈለጎት ወይም የሚያሳስቦት ነገር ካለ፣ እባክዎን ወደጡት ማጣሪያ ምርመራ መርሃ ግብር (Breast Screening Program) ይደውሉ።.**

**ዊኒፔግ** (Winnipeg)፡ 788-8000
**ብራንደን** (Brandon) 578-2040
**ከክልል ውጭ** (Long Distance) 1-800-903-9290
www.cancercare.mb.ca/MBSP/

## የጡት ጤናን ወይም የጡት ነቀርሳን በተመለከተ፣ ተጨማሪ መረጃ ከየት ማግኘት እችላለሁ?

**CancerCare Manitoba Breast Cancer Centre of Hope**
691 Wolseley Avenue
Winnipeg MB R3G 1C3
788-8080 ወይም 1-888-660-4866.ይደውሉ።
www.cancercare.mb.ca/Hope/

ማእከሉ አሳሳቢ የጡት ሁኔታ ላለው ወይም ሕይወቱ በጡት ነቀርሳ ለተነካ ማንኛውንም ሰው ይረዳል። መረጃ፣ እገዛ እና እርዳታ እንዲያገኙ አገልግሎት ይሰጣል። ይህም በስልክ ወይም በአካል በመምጣት ሊከናወን ይችላል።

እርስዎ ማድረግ የሚችሉት፣

- ምርመራዎችንና አስተያየቶችን ለመረዳት ከነርስ ጋር መገናኘት
- አቻ ድጋፍ ወደሚሰጡ በጎ ፈቃደኞች መመራት
- ሙያዊ ምክር ወደሚገኝበት መመራት
- የሚያውስ ቤተ-መጻሕፍትን መጎብኘት
- የመረጃ በራሪ ወረቀት መፈለግ
- ጥቅም ላይ የዋለ የሰው-ሰራሽ አካል ባንክን መጠየቅ
- የማዕከሉን ዜና-ነክ ጽሑፍ መቀበል
- በገጠር እና በሰሜን ማኒቶባ ውስጥ የሚገኙ አገልግሎቶችንና የእገዛ አውታሮችን ማፈላለግ ነው።

All translated materials completed in partnership with
Sexuality Education Resource Centre
February 2010

# ከጉብኝትዎ በኋላ

MANITOBA BREAST SCREENING PROGRAM

ማኒቶባ የጡት ማጣሪያ ምርመራ መርሃ ግብር

www.cancercare.mb.ca/MBSP/
Amharic
CancerCare MANITOBA

## ከጡት ማጣርያ ምርመራ ቀጠሮዬ በኋላ ምን ይሆናል?

ከጉብኝትዎ ቀጥሎ ባሉት ቀናት ውስጥ፣ ራጂ የሚያነሳ ባለሙያ (የራጂ ሐኪም) የጡት ራጂዎን (‘ማሞግራምዎን’) ይመረምራል። ማሞግራምዎ ጤናማ መሆኑን ወይም ተጨማሪ ምርመራዎች የሚያስፈልግዎት ከሆነ ይወሰናል። በመርሃ ግብራችን ከተሳተፉት ሴቶች መካከል፣ ከ93 እጅ በላይ ጤናማ ውጤቶች አሏቸው። ለተጨማሪ ምርመራዎች ከሚላኩት ሴቶች መካከል፣ አብዛኞቹ የጡት ነቀርሳ አይኖርባቸውም።

## የምርመራ ውጤቶቼን አገኛለሁ?

በሁለት ሳምንት ውስጥ የማሞግራም ውጤቶችዎ ለእርስዎና ለሐኪምዎ በማኒቶባ የጡት ማጣሪያ ምርመራ መርሃ ግብር ይገለጽላችኋል። ያለፉ ማሞግራሞችዎን ከሌላ ክሊኒክ መጠየቅ ካለብን፣ አንዳንድ ጊዜ መዘግየት ይኖራል።

## ከማሞግራሙ ምርመራ በኋላ፣ ችግሮች ይኖሩኛል?

ኣብዛኞቹ ሴቶች ከምርመራቸው በኋላ ችግሮች አይኖሩባቸውም። አንዳንድ ሴቶች፣ በጥቂት ቀናት የሚጠፋ የመቅላት ወይም የመበለዝ ምልክት ሊኖራቸው ይችላል። ከጡቱ ስር በጡት መያዣ መስመር ያለው ቆዳ በጣም ከመሳሳቱ የተነሳ፣ አንዳንድ ጊዜ የመቀደድ ሁኔታ ሊያጋጥም ይችላል። አካባቢውን ንጹህና ደረቅ አድርጎ መያዝ፣ ለመዳንና የወደፊት ችግሮችን ለመከላከል ሊረዳ ይችላል።
የቆዳ ሽፍታ ኢንፌክሽን ወይም የማይጠፉ ችግሮች በጡቶችዎ ላይ ካሉዎት፣ የጤና ባለሙያዎን ያነጋግሩ።

## ሁሉም የጡት ነቀርሳዎች በማሞግራም ሊታዩ ይችላሉ?

ከአስር የጡት ነቀርሳዎች ውስጥ በግምት ሁለቱ በማሞግራም ሊታዩ አይችሉም። ስለዚህም፣

- ጡቶችዎን በየጊዜው በጤና ባለሙያዎ ማስመርመር
- ጡቶችዎ በተለምዶ የሚመስሉትንና ያሉበትን ሁኔታ በዳሰሳ ማወቅ
- በየጤና ምርመራዎቾ መካከል በጡቶችዎ ላይ ማንኛቸውንም ለውጥ ካዩ፣ የጤና ባለሙያዎን ማሳወቅ።

## ለቀጣይ ምርመራ መቼ መመለስ አለብኝ?

ኣብዛኞቹ ሴቶች **በሁለት** ዓመታት ውስጥ ወደ መርሃ ግብሩ እንዲመለሱ ይጠየቃሉ።

አንዳንድ ሴቶች **በአንድ** ዓመት ውስጥ እንዲመለሱ ሊጠየቁ ይችላሉ። ለዚህም፣ በአብዛኛው የተለመዱት ምክንያቶች፣

- በዘር ጠንካራ የጡት ወይም የማህጸን ነቀርሳ (ovarian cancer) ታሪክ ካሎት።
- በራጂው ግምገማ ውጤት መሰረት፣ ባለሙያው በየጊዜው ያለማቋረጥ መምጣት ለእርስዎ የተሻለ እንደሚሆን ሲያስብ።
- የመጀመሪያ ጊዜዎ በመሆኑና ለማወዳደርም ሌላ የራጂ (x-ray) ፊልሞች ስለሌሉን ነው።

የሚቀጥለው ቀጠሮዎ መቼ እንደሆነ የሚያስታወስ ደብዳቤ እንልክልዎታለን። ደብዳቤው ካልደረስዎት ግን እባክዎን ይደውሉልን።

## ተጨማሪ ምርመራዎች እንደሚያስፈልጉኝ በደብዳቤዬ ላይ ከተገለጸ፣ ምን ማድረግ አለብኝ?

ለተጨማሪ ምርመራ ከሚሄዱት 10 ሴቶች መካከል፣ ዘጠኙ የጡት ነቀርሳ <u>እንደማይኖራቸው</u> ማወቅ አስፈላጊ ነው። ተጨማሪ ምርመራዎች፣ የመደበኛው የማጣሪያ ምርመራ አንዱ ክፍል ናቸው። አብዛኛውን ጊዜ ላልተለመዱ ውጤቶች ምክንያት የሚሆኑት ነቀርሳ ያልሆኑ የጡት ምልክቶች (benign) ሲታዩ ነው።

ተጨማሪ ምርመራዎች ለሚያስፈልጋቸው ሴቶች፣ ተጨማሪ መረጃ ከደብዳቤአቸው ጋር ወይም በስልክ ይነገራቸዋል። ተጨማሪው ምርመራ በሁለት መንገዶች ይዘጋጃል፣

- በጤና ባለሙያዎ <u>ወይም</u>
- በጤና ባለሙያዎ ፈቃድ፣ የጡት ማጣሪያ ምርመራ መርሃ ግብር ቀጠሮ ያስይዝሎታል። የቀጠሮዎን ቀንና ሰዓት በስልክ እንነግሮታለን።

## ምን ዓይነት ምርመራዎችን መውሰድ ይገባኛል?

አብዛኞቹ ሴቶች፣

- የጡት የጤና ሁኔታ ምርመራ ማሞግራም ወይም
- የውስጥ አካል መመርመሪያ መሳሪያ ‘አልትራሳውንድ” ያስፈልጋቸዋል።

**ዲያግኖስቲክ ማሞግራም** የሚጠቀመው አሳሳቢ የሆነውን አካባቢ በቅርብ ለማየት ነው።

- በጡት ውስጥ በሚገኝ የሴሎች ክምችት ውስጥ ትንሽ አክባቢን አሳስቶ በበለጠ ጥራት ለማየት፣ ተጨማሪ ግፊትን ይጠቀማል።
- በጡት ውስጥ በሚገኝ የሴሎች ክምችት ውስጥ ያለውን አከባቢ አጉልቶ ማሳየት ይችላል።

**አልትራሳውንድ** የጡትዎን ስእል ለማንሳት የድምጽ ሞገድን ይጠቀማል። አልትራሳውንድ ውሃ በቋጠሩ እብጠቶች (በፈሳሽ የተሞሉ ጉዳት የማያስከትሉ ከረጢቶች) እና ባልተለመዱ ሌላ ዓይነት እባጮች መካከል ያለውን ልዩነት ያሳያል።

## እነዚህን ምርመራዎች በማኒቶባ ውስጥ የት አገኛለሁ?

ከሚከተሉት ቦታዎች ወደ አንዱ ሊመሩ ይችላሉ፣

ዊኒፔግ (Winnipeg)፡
- WRHA Breast Health Centre
- Health Sciences Centre
- Manitoba X-ray Clinic
- Radiology Consultants of Winnipeg
- St Boniface General Hospital

ብራንደን (Brandon)፡
- Brandon Regional Health Centre